# የካቢኔ ለውጡ ለገጠመን ችግር በጥራትና በፍጥነት መልስ ለመስጠት ያግዛል

ዶ/ር አረጋ ይርዳው



ዶ/ር አረጋ ይርዳው በአሁኑ ወቅት 24 የተለያዩ ኩባንያዎችን የሚያስተዳድረው የሚድሮክ ቴክኖሎጂ ግሩፕ ቺፍ ኤግዚኪዩቲቭ ኦፊሰርና የዩኒቲ ዩኒቨርስቲ ፕሬዚደንት ናቸው። ከወቅታዊ ሀገራዊ እና ዓለምአቀፍ ጉዳዮች ጋር በተገናኘ ከባልደረባችን ፍሬው አበበ ጋር ያደረጉት ቃለምልልስ እንደሚከተለው ተስተናግዷል።

**ሰንደቅ፡- የኢትዮጵያ ፓርላማ በቅርቡ በጠ/ሚኒስትሩ አቅራቢነት አዲስ የካቢኔ አባላትን ሹመት አጽድቋል። በዚህ ሥነሥርዓት ላይ ከተጋበዙ እንግዶች አንዱ እንደመሆንዎት ሹመቱን እንዴት አዩት?**

ዶ/ር አረጋ፡- የተመረጡት ሰዎች የነበራቸውን የትምህርት ዝግጅትና የኋላ የሥራ ልምድ ታሪካቸውን ሲነገር በጥሞና አዳምጫለሁ። ለውጥ ምንጊዜም ቢሆን አስፈላጊ ነው። የዓለምም ሁኔታ እንዲሁ ተለዋዋጭ ነው። በሀገራችን በቅርብ ጊዜ ገጥሞን በነበረው አንዳንድ ያለመረጋጋት ችግሮች ከመፍቻ ስልቶች አንዱ የጠ/ሚኒስትሩን ካቢኔ መመልከትና አንዳንድ ለውጦች ማድረግ መሆኑ በመንግሥት በኩል ተወስኖ፣ ይህን ለመፈፀም የተደረገውን ጥረት አደንቃለሁ። በአጭሩ በአሁኑ ሰዓት በትምህርት ደረጃ ብቃት ሁሉም በሚባል ደረጃ የተማሩ ሰዎች የተሳተፉበት ካቢኔ ተመስርቷል። ካቢኔው ከመጀመሪያ ዲግሪ ጀምሮ እስከ ፕሮፌሰር ደረጃ ያሉ ሰዎች ስብጥር የያዘ ነው። ከተመልካች አኳያ ሂደቱን ስገመግመው የጠ/ሚኒስትሩ «በአማካሪነት» ደረጃ የተቀመጡ ቦታዎችን መሰረዛቸውና በሁለተኛ ደረጃ «ክላስተር» የሚለው አደረጃጀት ምንም እንኳን በቡድን ሥራዎችን ተከፋፍሎ ለመሥራት የሚያመች ቢመስልም ምናልባትም በተግባር ከታየ በኋላ ይሄ ቢቀር ይሻላል የሚል ውሳኔ ማሳለፋቸው መልካም ሆኖ ነው ያየሁት። ከሕገመንግሥት አኳያ ተጨማሪ ሁለት ም/ጠቅላይ ሚኒስትሮች መኖራቸው በአንዳንድ ወገኖች ዘንድ ሕጋዊ ነው፣ አይደለም የሚል ክርክሮችን ሲያስነሳ መቆየቱን ታዝቤአለሁ። በእኔ አረዳድ ቀደም ሲል በነበረውም አደረጃጀት ቢሆን የማውቀው አንድ ምክትል ጠ/ሚኒስትር መሾሙን ነው። ሌሎቹ በምክትል ጠ/ሚኒስትር ማዕረግ እንጂ ምክትል ጠ/ሚኒስትር ናቸው አልተባለም። ይህም ሆኖ ይህ አደረጃጀት ቀርቶ አንዳንድ ሥራዎች በኮሚቴ ደረጃ ለመሥራት ጠ/ሚኒስትሩ መወሰናቸው ከነበረው የተሻለ አቀራረብ ነው ብዬ አምናለሁ።

በተጨማሪም በዕለቱ በፓርላማ መድረክ በጥሩ ጎኑ ያየሁት የተማሩ ሰዎች በካቢኔ ውስጥ የመካተታቸው ጉዳይ ነው። ከዚህ በፊት መንግሥትን በተደጋጋሚ ስንመክር የቆየነው ሰዎች ሲመደቡ በችሎታቸው፣ ባላቸው ልምድ ቢሆን ይሻላል እያልን ነበር። የፓርቲ አባል መሆን ወይንም የአንድ ሃይማኖት ተከታይ መሆን ከሥራ ጋር መገናኘት የለበትም። የፓርቲ አባል ሆነው የተማሩና ብቃቱ ያላቸው ሰዎች ሲመደቡ ነበር፤ ይህ ትክክል ነው። በተጨማሪም ከፓርቲ አባልነት ውጪ ያሉ አንዳንድ ሰዎች መካተታቸው ጥሩና ፈር ቀዳጅ ይሆናል ብዬ አምናለሁ። ለምሣሌ በአሜሪካን ሀገር አሁን በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት ዲሞክራት ነው። በሥልጣን ዘመኑ በሹመት ወቅት ብቃት ያለው ከሆነ የሪፐብሊካን ፓርቲ አባል የሆነን ሰው ሳይቀር አምጥተው ይሾማሉ። ይሄ ሰውየውን ከሞያውና ከሥራው አኳያ መመልከት እንጂ ከፓርቲ አባልነት አኳያ ብቻ መመልከት ተገቢ አለመሆኑን የሚያሳይ ነው። በካቢኔው ውስጥ የተማሩ ሰዎች በብዛት መኖራቸው ቢያንስ፣ ቢያንስ ከክህሎትና ከትምህርት ማነስ የተነሳ የሚመጣ ችግር ከጅምሩ ለማስወገድ ያስችላል። መማር ብቻውን ሥራ ይሠራል ማለት ሳይሆን መማር ሥራዎችን ለመሥራት የተሻለ እገዛ ይሰጣል ብሎ ማመኑ ጥሩ ይመስለኛል። በሌላ በኩል ደግሞ መጠንቀቅ ያስፈልጋል። ዲግሪ ያለው ብቻ ነው የተሻለ ሥራ ማከናወን የሚችለው የሚል አስተሳሰብ መፈጠር የለበትም። ሥራን ለመሥራት ትምህርት አስፈላጊ መሆኑ ባያጠራጥርም ዲግሪ የሌላቸውም ሰዎች ከፍተኛ የሆነ ሥራ ማከናወን እንደሚችሉና እያከናወኑም እንደሆነ መዘንጋት የለበትም። በየትኛውም እርከን ሥራን ማቀላጠፍ የሚችለው በከፍተኛ ደረጃ የተማረ ብቻ ነው የሚል አስተሳሰብ ተፈጥሮ ችግር ውስጥ እንዳይከተን መጠንቀቅ ተገቢ ነው።

በተጨማሪም ጠ/ሚኒስትሩ የፓርላማ ውክልና ጉዳይ መስተካከል እንዳለበትና አስፈላጊ ከሆነ ሕገመንግሥቱን እስከማሻሻል መሄድ እንደሚቻል ደፈር ብለው የተናገሩትን

ወደ ገፅ 19 ዞሯል

# የካቢኔ ለውጡ ለገጠመን ችግር...

አደንቃለሁ። ይሄ ውሳኔ ለኢትዮጵያ ትልቅ እርምጃ ይሆናል ብዬም አምናለሁ። አሁን የምርጫ ሕጉ ከተለወጠ ፓርላማ ውስጥ ብዙ ሰዎች የመወከል እድላቸው ይሰፋል ማለት ነው። ይህም ሆኖ ግን ቁጥራቸው ብዙ የሆኑ ፓርቲዎች መኖራቸው እንከን አለው ብዬ አምናለሁ። ለምሣሌ 50 ፓርቲዎች አሉ ከተባለ፤ የሚያቀርቧቸው የጋራ አጀንዳዎች፣ የተወሰነ ልዩነት ቢኖር እንኳን ያንን ወደጎን አድርገው ጠንከር ወደአሉ ሁለት እና ሶስት ፓርቲዎች መሸጋሸጉ (መዋሃዱ) ትልቅ ጥቅም አለው ብዬ አምናለሁ። ፓርቲዎች በመብዛታቸው ምክንያት መራጩ ሕዝብ ልዩነታቸውን ለማየት ይቸገራል። አሜሪካንን ብትወስደው ሶስት ፓርቲ አለ፤ ሌሎችም በሰፊው የማይታወቁ አሉ። ግን የሁለቱን ትልልቅ ፓርቲዎች (ዴሞክራት እና ሪፐብሊካን) ልዩ ባህሪይ ሕዝብ በቀላሉ ያውቃል። ፓርቲዎች ሲበዙ አንዱ ከሌላው የሚለይበትን ለማወቅ ያዳግታል።

የተቀናቃኝ ፓርቲዎች የምርጫ ሕጉ ከተሻሻለ እርስ በርስ ያላቸውን ልዩነት አጥበበው፣ የሚታረቀውን አርቀው፣ በአማራጭነት ለመቅረብ መዘጋጀት አለባቸው ብዬ አስባለሁ።

ሌላው "ተቃዋሚ" (ኦፖዚሽን ፓርቲ) የሚባለው አጠራር ትክክል አይመስለኝም። ተቀናቃኝን ተፎካካሪ ማለት ይሻላል። ተቀናቃኝ ፓርቲ ከሆንክ የምትቃወመውን ትቃወማለህ፣ የምትደግፈውን ትደግፋለህ፣ የሚሻሻለውን እንዲስተካከል ሃሳብ ትሰጣለህ። ሥራህ መቃወም ብቻ ከሆነ ትክክል ነው ብዬ አላምንም። እናም ፓርቲዎችን በሕጋዊ ስማቸው መጥራት ያስፈልጋል። ተቃዋሚ (ኦፖዚሽን) ፓርቲ በማለት መፈረጅ የለብንም። የምንጠብቀው በአንዳንድ ጉዳዮች ልዩነት ቢኖራቸውም በብዙ ነገር በጋራ ተባብረው ለሀገር እንዲሠሩ ነው የሌላው ሀገር ተሞክሮም ይህ ነው።

በጥቅሉ የምርጫ ሕጉ ከተሻሻለ ፓርቲዎቹ ያላቸውን ልዩነት አጥብበው፣ ቁጥራቸውን ትንሽ አድርገው አጀንዳቸውን ለሕዝብ የሚያቀርቡበት ሁኔታ መፍጠር አለባቸው። በዚህ ሁኔታ ወደምርጫ ሲገባ ሕዝቡ ግልፅ የሆነ አማራጭ ይኖረዋል። በዚህ መልክ የፓርላማ ወንበር ከተገኘ ገዢው ፓርቲም ይሁን ተቀናቃኝ ፓርቲዎች የሕዝብ እሮሮና አስተሳሰብ በፓርላማ መድረክ ለማቅረብ ይችላሉ። ሕዝቡ ኀሳቡን የሚገልፅበት አጥቶ በቁጣ እስኪገነፍል የሚያደርሰው ነገር በእጅጉ ይቀንሳል።

**ሰንደቅ:- በገዢው ፓርቲ እና በተቀናቃኝ ፓርቲዎች መካከል ከመቀራረብ ይልቅ ተራርቆ መፈራረጅ፣ በሚያግባባ ጉዳይ እንኳን ለመነጋገር፣ አብሮ ለመሥራት ያለመቻል፣ አንዳንዴም በጠላትነት የመተያየት አዝማሚያዎች በስፋት ይታያሉ። በዚህ ጉዳይ ላይ አስተያየትዎ ምንድነው?**

ዶ/ር አረጋ:- በዚህ ረገድ ከሁለቱም በኩል ስህተት አለ ብዬ አምናለሁ። በዚህ ሁኔታ ወደየት ነው የምንሄደው ብሎ መጠየቅ ይገባል። የተለያዩ ፓርቲዎች የሆኑበትን ወይም ዓላማ ጠንቅቆ ማውቅ ያስፈልጋል። የሃሳብ ልዩነት መኖሩ፣ ከሃሳብ ፍጭት ጥሩ ነገር ሊገኝ እንደሚችል ማመኑ፣ ሁሉም ፓርቲዎች ለአንድ እናት ሀገር እድገት እንደሚያስቡ ማመን ያስፈልጋል። የሃሳብ ልዩነት መኖሩ ጥሩና ተፈጥሮአዊ ነው። የተሟሟቀ ክርክርና ውይይት አስፈላጊ ነው። መጨረሻ ላይ ግን የእኔ ኀሳብ ጥሩ ነው። የአንተ ሃሳብ የበለጠ ጥሩ ነው በሚል ድምዳሜ ወደመግባባት ላይ መደረስ መቻል አለበት። ይሄን ለማድረግ ሁሉም ወገን መጣር ይኖርበታል፤ ጊዜ ይፍጅ እንጂ ይህ አስተሳሰብና አሠራር አይቀርም።

አብዛኛውን የፓርላማ መቀመጫ ያሸነፈው ወገን ገዢ እንደመሆኑ መጠን የራሱን አጀንዳ ማራመድ ይፈልጋል። ይሄ መሆኑ ትክክል ነው። የትም ሀገር ብትሄድ ተመሳሳይ አካሄድ ነው የምታገኘው። በአሜሪካን ሀገር አሁን ሪፐብሊካኖች አሸንፈዋል፣ የራሳቸውን አጀንዳ ነው ማራመድ የሚፈልጉት። ዲሞክራቶቹ ደግሞ በሚስማሙበት ጉዳይ ላይ አብረው ይሰራሉ፣ የማይስማማቸው ሲሆን ደግሞ በድምፃቸው አልተስማማንም ይላሉ። ሪፐብሊካኖቹ የሚሠሩትን በሙሉ ዲሞክራቶቹ እንቃወማለን ቢሉ የሚገኝ ነገር የለም። በእኛ ሀገር ፖለቲካም ቢሆን አሸናፊው ገዢ ፓርቲ ሊጠነክር የሚችለው ሌላ ሃሳብ ያለው ቡድን እንዲኖር ሲያደርግ ብቻ ነው። ተቀናቃኞቹም ደግሞ ገዢው ፓርቲ የሚሠራውን በሙሉ ስህተት ነው ብሎ በመናገር መጓዝ ሣይሆን ገዢው ፓርቲ የሠራቸውን ጥሩ ነገሮች በመቀበልና በማሞገስ ትክክል ያልሆነውን ደግሞ ከመቃወምም ባሻገር በዚህ መንገድ መሠራት ነበረበት፣ ይህ አማራጭ አለ የሚለውን በማቅረብ የበኩላቸውን አዎንታዊ ሚና መወጣት አለባቸው። ስለዚህ እስከዛሬ የነበረው መጠላላት፣ መፈራረጅ የሂደት ጉዳይ እንጂ እየተቀረፈ መሄዱ የማይቀር ነው። አሜሪካኖች አሁን የደረሱበት ደረጃ የደረሱት ብዙ ውጣ ውረዶችና ፈተናዎችን አልፈው ነው። በአሜሪካን ሀገር በእኛ ዕድሜ ነው፤ ሴቶች እንኳን የመምረጥ መብት ያገኙት። ስለዚህ በፖለቲካ ሂደት ችግሮች ማጋጠማቸው እንግዳ ነገር ሊሆን አይገባም። ችግሮችን ግን በሰለጠነ መንገድ፣ በፍጥነት እየፈቱ መሄድ እድገትን ከማስቀጠል አኳያ አስፈላጊ ነው።

**ሰንደቅ:- ሀገሪቷ ውስጥ ብዙ ችግሮች አሉ። ሌላውን ትተነው ገዢው ፓርቲ ራሱ ያመነባቸው የመልካም አስተዳደር፣ የሙስናና ብልሹ አሠራር ችግሮች የመቅረፍ ትልቅ የቤት ሥራ አለ። አዲሱ ካቢኔ ይህን ሁሉ ውዝፍ ችግሮች በአጭር ጊዜ ይወጣዋል ብለው ያምናሉ?**

ዶ/ር አረጋ:- በእኔ እምነት አሁን የተደረገው የካቢኔ ለውጥ ለገጠመን ችግር በጥራት እና ፈጠን ባለመልክ ለመሥራት ክህሎቱ፣ ዕውቀቱ፣ ልምዱ ያላቸው ሰዎች ስብሰብ ነው ብዬ አምናለሁ። መሥራት ከሚችሉት በላይም መወጠር የለባቸውም። ስለዚህ ዋና ዋና ጉዳዮች ናቸው የሚባሉትን ችግሮቹን በቅደም ተከተል ለመፍታት ጥረት ማድረግ አለባቸው።

በፓርላማ ከሰማሁት መካከል ከወጣቶች ቁጥር መብዛት ጋር ተያይዞ በሚፈለገው ደረጃ ሥራ መፍጠር አለመቻሉ መታመኑና መነገሩ ለመፍትሄው ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል። ሀገራችን የወጣቶች ሀገር ናት። ሀገራችን ብዙ ዩኒቨርሲቲዎች ከፍታ ወጣት ተማሪዎችን እያስተማረች ነው። ከት/ቤት ተምረው የሚወጡ ወጣቶች ተምረዋልና ሥራ ማግኘት ይፈልጋሉ። ባለፉት ዓመታት መንግሥት እነዚህን ወጣቶች ሥራ ለማስያዝ የሚያደርገው ጥረት ከፍተኛ ቢሆንም በሥራ ፈላጊው እና በቀጣሪዎች ወይም በፍላጎትና አቅርቦት አለመጣጣም ምክንያት ውጤቱ የሚፈለገውን ያህል አርኪ አልሆነም። ይህ የፍላጐትና የአቅርቦት አለመጣጣም ችግር ወደፊት ሊቀጥል እንደሚችል መገመት ይቻላል። ስለዚህ ይህን ችግር ለማቃለል ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። የፍላጎትና አቅርቦት አለመጣጣም የሚቀጥል ከሆነ ምንጊዜም ይህ ሁኔታ የችግር ምንጭ ሆኖ መቀጠሉ የሚቀር አይደለም። በአሁኑ ጊዜ ያለወጣት በእኔ ዕድሜ ከነበረ ወጣት የተለየ ነው። የአሁኑ ወጣት ዓለም አቀፋዊ አስተሳሰብ የያዘ ነው። ስለዓለም ብዙ ያውቃል። ራሱን ማሻሻል፣ መማር፣ ማደግ የሚፈልግ አልፎ ተርፎም ወደአደጉት ሀገራት ሄዶ መሥራትና ራሱንና ቤተሰቡን ማሻሻል የሚፈልግ ነው። ይሄ ዓይነት ወጣት በእኔ ጊዜ ከነበረውና በይበልጥ ናሽናሊስት ነኝ ከሚለው ወጣት የተለየ ነው። ይህን ተረድቶ የወጣቶችን ጥያቄ ለመመለስ በትኩረት መንቀሳቀስ ያስፈልጋል። መንግሥትም ለዚህ አቢይ ጉዳይ ልዩ በጀት አድርጎ ችግሩን ለመቅረፍ መነሳቱ የሚደገፍ ውሳኔ ነው። በዚህ መንገድ ችግሩ ሙሉ በሙሉ መፍትሄ ያገኛል ወይ ከተባለ ሊገኝም፣ ላይገኝም ይችላል። ዋናው ነገር የወጣቱ ጥያቄ ትኩረት አግኝቶ መልስ ለመስጠት ሁልጊዜም ሳያቋርጡ ጥረት ማድረጉ ላይ ነው።

ሌላው ችግር በሥራ ላይ ያየነው በፕሮፌሽናል ወይም በሙያተኞች ያለማመን ጉዳይ ቀደም ሲል ይታይ ነበር። በአሁን ሰዓት ይህ በየደረጃው ይታይ የነበረ ችግር እርምት እያገኘ መሆኑ ጥሩ ነገር ነው። በካቢኔ ደረጃ ያለው ጅምር ወደታች ባሉ የመንግሥት እርከኖች መውረድ አለበት። እናም ሙያው ያላቸው እያሉ የፓርቲ አባል መሆን ወይም በሌላ ምክንያት ቦታውን ብቁ ያልሆነ ሰዎች ከያዙት ጉዳቱ የሀገር መሆኑን አለመዘንጋት ጥሩ ነገር ነው።

**ሰንደቅ:- እንደሚታወቀው ወደሀገር ቤት ጠቅልለው ከመምጣትዎ በፊት በአሜሪካን ሀገር ለረጅም ዓመታት ኖረዋል። የሰሞኑ የዩናይትድስቴትስ አሜሪካ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ውጤት እንዴት አገኙት?**

ዶ/ር አረጋ:- ከአሜሪካን ሀገር ወደ ሀገሬ ከተመለስኩኝ 16 ዓመታት ገደማ ሞላኝ። በዚህ መካከልም አንድ ሁለት ምርጫዎች አይቻለሁ። እኔ ወደአሜሪካ በሄድኩበት ወቅት የነበሩት ፕሬዚዳንት ሬገን ነበሩ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከአሁኑ ፕሬዚዳንት ትራምፕ ድረስ የምርጫ ሁኔታዎችን፣ የፖለቲካ አካሄዶችን እጅግ እከታተላለሁ፣ አነባለሁ። የማላደርገው ፖለቲካ ውስጥ ገብቼ መሥራት ነው። ፖለቲካውን መከታተልና መገምገም ለብዙ ዓመታት እንደሆቢ አድርጌ ይዤዋለሁ (እወደዋለሁ ማለቴ ነው)። የአሜሪካ ምርጫ ለየት ያለ ሂደት ነው ያለው። ኤሌክቶራል ኮሌጅ (Electoral college) የሚባል ልዩ የምርጫ አሠራር አለበት። ይሄ የምንሰማው 270 የምርጫ ማሸነፊያ የቁጥር ውጤት ምን ማለት ነው የሚለውን ማወቅ ይገባል። አሜሪካኖች ፓፑላር ቮት (Popular vote) እና ኢሌክቶራል ኮሌጅ የሚባለው አሠራራቸውን በደንብ ማወቅ ጥቅም አለው። በአሜሪካ 50 ግዛቶች (ስቴትስ) አሉ እንበል። ከእነዚህ ግዛቶች እንደካሊፎርኒያ ዓይነቱ ወደ 30 ሚሊዮን ሕዝብ ቢኖረው ሌላ አነስ ያለው ግዛት ደግሞ 2 ወይም 3 ሚሊዮን ሕዝብ ቢኖሩት፣ ዝም ብሎ በእያንዳንዱ ሰው ድምፅ (one man one vote) ቢኬድ ኖሮ ተለቅ፣ ተለቅ ያለ ቁጥር ያላቸው ግዛቶች ያሸነፈው ፕሬዚዳንት ይሆናል ማለት ነው። ስለዚህ አሜሪካኖች ይህ ዓይነቱ የድምፅ አሰጣጥ አደገኛ ነው፣ ትናንሽ ግዛቶችን ድምፅ አልባ ያደርጋል አሉና አካሄዱን ኤሌክቶራል ኮሌጅ በመጨመር አጠናከሩት። በዚህ ኤሌክቶራል ኮሌጅ አሠራር ግዛቶች እንደ ህዝባቸው ብዛት ቁጥር ተመድቦላቸዋል። ለምሳሌ ካሊፎርኒያ 55 ኤሌክቶራል ቁጥር ተመድቦለታል። ሌሎችም እስከ 3 ቁጥር የተመደበላቸው አሉ። ታዲያ ፕሬዚዳንት ለመሆን ቁጥሮቹን ከየግዛቶቹ በማግኘት 270 ድረስ አሸናፊ ያደርጋል።

በፖፑለር ቮት ወይም እያንዳንዱ ሰው በሚሰጠው ድምፅ ብቻ ምርጫው ከተካሄደ ትናንሾቹ ግዛቶች ስለሚደመሰሱ እያንዳንዳቸው የኢሌክቶራል ቮት እንዲሰጣቸው ተደረገ፤ በመሆኑም 270 ወደተባለችው ፕሬዚዳንትነትን የምታስገኘውን ቁጥር ላይ ለመድረስ ተወዳዳሪው ሁሉንም ግዛቶች የማስታወስና ድጋፍ የመጠየቅ ጥረት ያደርጋል። በዚህ አካሄድ ባለፉት 44 የአሜሪካን ፕሬዚዳንቶች ውስጥ በፖፑለር ቮት (በህዝብ ምርጫ) አሸንፈው ፕሬዚዳንት ያልሆኑ 5 ሰዎች አሉ። አልጎር አንዱ ናቸው፣ አሁን ደግሞ ሂላሪ ክሊንተን ሌላዋ ናቸው። በመራጭ ቁጥር ብዛት (ፖፑላር ቮት) ቢሆን ኖሮ ሂላሪ አሸንፈው ነበር። ግን በኤሌክቶራል ኮሌጅ ሲወሰድ ትራምፕ አልፎ ሄደ። ሂላሪ 270 ሊደርሱ አልቻሉም። እናም ይህቺ የምርጫ አሠራር በእኛም ሀገር አነስ ያሉ ክልሎች እንዳይጎዱ ልንጠቀም የምንችልበት ሁኔታ ስላለ ቢያንስ አሠራሩ ቢጠና ጥሩ ነው።

ወደምርጫው ውጤት ስመለስ የሚስተር ዶናልድ ትራምፕ መመረጥ ብዙ ሰዎችን አስደንቋል። እኔ ግን ከመጀመሪያው ጀምሮ የትራምፕ ደጋፊ ስለነበርኩኝ ማሸነፋቸው አላስገረመኝም። በእኔ ዕይታ ብዙ ሰዎች ትራምፕ ትክክል አይደለም ብለው ያሰቡት በምርጫ ውድድር ወቅት የተናገሩትን በመውሰድ ነው። በምርጫ ውድድር ወቅት በአሜሪካን ሀገር ብዙ ነገር ይነገራል። የአነጋገር ስልት ያላቸው ዕጩ ፕሬዚዳንቶች አሉ፣ የሌላቸውም አሉ። ትራምፕ ከፖለቲካው ዓለም ያልመጡ ባለኃብት ኢንቨስተር/ነጋዴ እንደመሆናቸው መጠን እንደፖለቲካ ሰዎች የሚጣፍጥ ቋንቋ እንዲናገሩ አይጠበቅም። ስለዚህ ግልፅ በሆነ መልክ፣ በሚመስላቸው ቋንቋ ለመናገር ሞክረዋል። ይሄ አንዱ ነው። አልፎ አልፎ ከእሳቸው የማይጠበቁ ነገሮችም ሲናገሩ ሰምተናል። በምርጫ ውድድር ጊዜ አሜሪካ ውስጥ በተቻለ መጠን የተቃዋሚን ጉድ በማውጣት ለማሸነፍ መሞከር የተለመደ ነው። ስለዚህ እሳቸው ድንበር እዘጋለሁ፣ ሙስሊም ወገኖችን እና ሕጋዊ ሠነድ/ዶክመንት የሌላቸውን የውጭ ዜጎችን አስወጣለሁ በሚሉበት ጊዜ ይሄ ዓይነት ነገር ደስ የሚለው ወገን ይኖራል። በእኔ ዕይታ ይህ የሰውየው አካሄድ የእነዚህን ሰዎች ድምፅ ለመውሰድ ነው። ነገር ግን በምርጫ ጊዜ የተነገረው ሁሉ ግን ትክክል ነው ወይም ይተገበራል ብሎ መውሰድ ግን አይቻልም። አሁን ሥልጣን ላይ ያሉት ፕሬዚዳንት ኦባማ ኩባ አካባቢ ያለውን ጓንታናሞ እስር ቤት እዘጋለሁ ብለው ቃል ገብተው ነበር፤ ነገር ግን እስከአሁን አልተዘጋም። ሌሎችም ብዙ ያልተፈፀሙ ጉዳዮች አሉ። ይህ የሚሆንበት ምክንያት በምርጫ ጊዜ ዕጩ ፕሬዚዳንቶች የፈለጉትን ቢሉም ሲመረጡ ከሶስቱ የመንግሥት አካላት የሚይዙት የአስፈፃሚውን ክፍል ብቻ በመሆኑ ነው። ፕሬዚዳንቱ በምርጫ ጊዜ የገባውን ቃል ብቻውን ሊሠራው አይችልም። ሕግ ተርጓሚውና ኮንግረሱ አሉ። ስለዚህ የተባለው ሁሉ ይፈፀማል ብሎ እርግጠኛ መሆን አይቻልም። ዶክመንት የሌለው ስደተኛ ሁሉ ነገ ጠዋት ሊባረር ነው፣ አሜሪካ ድንበሯን ልትዘጋ ነው የሚለው በግሌ በቀላሉ የሚሆን ነው ብዬ ለመውሰድ እቸገራለሁ። ወንጀለኞች ላይ ግን ልዩ ትኩረት ይደረግ ይሆናል። ስለዚህ ሰውየው ምርጫውን ለማሸነፍ የሚሉትን ብለዋል። በዚያ ምክንያት ትክክል ናቸው፣ አይደሉም ብዬ መገምገም አልፈለኩም። ከዚያ ራቅ ያለውን ነገር ነው ማለት ያለብን። በብዛት የአሜሪካን ሕዝብ የሚያውቀው የእነኬኔዲ፣ የእነቡሽ፣ የእነክሊንተን የሥልጣን ዘመንን ነው። ሥልጣን ላይ በብዛት የምታያቸው ሰዎች የሕግ ምሩቃን፣ ጠበቃዎችና የመሣሠሉት ናቸው። በእኔ እምነት ሂላሪ ክሊንተን ቢያሸንፉ ኖሮ ክስተቱ ለሴቶች ትልቅ ምዕራፍ ይከፍት ነበር። በታሪካዊነቱ ቆንጆ ነበር። በሌላ በኩል ትራምፕ በማሸነፋቸው ሌላ ታሪክ ተፈጥሯል ብዬ አምናለሁ። በአሜሪካ ሀገር ውስጥ በመንግሥት ሥራና በወታደርነት ያልተሳተፈ ነጋዴ ግለሰብ ሁዋይት ሀውስ (ቤተመንግሥት) ገባ ማለት ራሱን የቻለ ትልቅ ታሪክ ነው። ምናልባትም ከዚህ በፊት አሜሪካ ውስጥ አንድ ጊዜ የተፈጸመ ይመስለኛል። አሜሪካ ውስጥ ግዙፍ ኩባንያዎችን የሚመሩ ወንዶችና ሴቶች አሉ። እነዚህ ለመመረጥ የገንዘብ አቅም ካላቸው ወደፊት በሩ ክፍት መሆኑን ትራምፕ አሳይተዋል። ይሄ ትልቅ ለውጥ ነው ብዬ አምናለሁ።

ሌላው የሚዲያው ወገንተኝነት አስገራሚና አነጋጋሪ ነበር። ትልልቆቹ መገናኛ ብዙሃን ሂላሪ 270 ሊገቡ ወይንም ሊያሸንፉ ጥቂት ነው የቀራቸው እያሉ እስከመጨረሻዋ ሰዓት ድረስ ያወሩ ነበር። ሚዲያው በዚህ አቋሙ ወደሂላሪ ያጋደለ፣ ወገንተኛ እንደነበረ ግልፅ ነው። ሚዲያው ይህ ሁሉ ኤክስፐርት ነኝ፣ ተንታኝ ባለሙያ ያሉት ሆኖ ይህን ዓይነት ስህተት እንዴት ሊሰራ ቻለ የሚለው አነጋጋሪ ሆኗል። የሚዲያው ዓላማ ሂላሪ እያሸነፉ ነው ብሎ በማወጅ ድጋፍ ለመስጠት ነው ወይንስ ሌላ ጉዳይ ነበረው? በበኩሌ እንደተከታተልኩት ሚዲያው ግልፅ ችግር እንደነበረበት ታዝቤአለሁ። በአሜሪካ የዘንድሮ ፕሬዚደንታዊ ምርጫ ዝም ያለው፣ ተገልያለሁ፣ ትኩረት ተነፍጎኛል ያለው የህብረተሰብ ክፍል ትራምፕን መርጧል ተብሎ ነው የሚገመተው። ይሄ ትልቅ ታሪክና ውጤት ይመስለኛል። ቀሪውን ዕድሜ ሰጥቶን በሥራ ሲተረጐም መመልከቱ ይበጃል።